የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፱ ቀን
፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.25
ADDIS ABABA, 8th January, 2016

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፰/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለፍትሐዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለጋራ ዕድገትና ተጠቃሚነት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማዕደቂያ አዋጅ……………ገጽ ፰ሺ፯፻፶

CONTENTS

Proclamation No.918/2015

International Development Association Financing Agreement for the Enhancing Shared Prosperity Through Equitable Service Program Ratification Proclamation …………………………………………page 8750

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፰//፪ሺ፰

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማኀበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ፍትሐዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለጋራ ዕድገትና ተጠቃሚነት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፬፻፴፩ ሚሊዮን ፭፻ ሺ ኤስ ዲ አር /አራት መቶ ሰላሳ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ህዳር ፳፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በህገ መንግስቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 918/2015

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANICING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOSIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit amount of 431,500,000 SDR (Four hundred thirty one million five hundred thousand Special Drawing Rights) for financing Enhancing Shared Prosperity through Equitable Services program was signed in Addis Ababa on the 22nd day of October 2015;

**WHEREAS**, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Financing Agreement at its session held on the 8th day of December 2015;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለፍትሐዊ መሠረታዊ አገልግሎት ለጋራ ዕድገትና ተጠቃሚነት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፰/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የልማት ማህበር መካከል ጥቅምት ፲፩ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 5716—ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፬፻፴፩ ሚሊዮን ፭፻ ሺ ኤስ ዲ አር /አራት መቶ ሰላሣ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቷል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበትጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፳፱ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Enhancing Shared Prosperity Through Equitable Service Program Ratification Proclamation No. 918/2015".

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit Number 5716-ET signed in Addis Ababa on the 22nd day of October 2015 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of 431,500,000 SDR (Four hundred thirty one million five hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Data

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this 8th day of January 2016**

**MULATU TESHOME (Dr.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**